# ፕሮፌሰር አለማየሁ ገ/ማሪያም !

# ሕዝብን መከፋፈል የወያኔ ነው

# አንተም እንደዚሁ እየሰራህ ነው!

ከተስፋሁን አበራ

ወያኔ በፍሽስታዊ ባህሪው፣ በዘረኛ ተፈጥሮው የተጠቀመበት ስትራቴጂ ሕዝብን ከሕዝብ፣ ሃይማኖትን ከሃይማኖት፣ድርጅት ከድርጅት በማጋጨትና በማናከስ ከፋፍሎና አዳክሞ አገርን ለባዕዳን በመሸጥ ሕዝብን የአገር ድሃ፣ ዜግነት አልባ አድርጐ ሃብቷን እየዘረፈ በኃይል እየገዛ ያለበት ዘዴ ነው። ድርጅት ከፈቱ ይልና በግድም በውድም የወያኔ ተለጣፊ ለመሆን ይገደዳሉ ።አንተ ደግሞ ተቆርቋሪ መስለህ ሕባችንን በዕድሜ ፣በአካል መጠን፣በጾታና በቁጥር ብዛት እየከፋፈልህና እየመደብህ፣ በእዱር አራዊት አምሳል ስም በመስጠት ቼታና ሂፖ ( cheetah & Hippo )ብለህ በማወክ ትገኛለህ። ይህ ሁሉ መላው ሕዝብ ለአገሩ ነፃነት፣ለመብቱና ለሕይወቱ፣ ለታሪኩና ለክብሩ ሁሉም በጋራ እንዳይታገል እንቅፋት ወጥመድ በመዘርጋት፣ወያኔዊ ሥራን እየተገበርክ ነው።ለኢትዮጵያና ለሕዝቧ ቀና አሳብ ከአለህ በረጋና ሁሉን በአመላከተ ኢትዮጵያን ማወቅ፣ ጥሩውን ከመጥፎው፣ እውነትን ከውሸት መለየትና ከፖለቲካ ወለምታ መዳን ነው። የፖለቲካ ውልግድግድ ወይም መዛባት (ኢንኰሬክት) እየፈጸምክ ነው።

አንድ የተማረ ሰው በጎሊናው ነሮችን አውጥቶ አውርዶ ከአገናዘበ፣ ከገመገመና ከተረዳ በኃላ በአንደበቱ አውጥቶ ተግባራዊ በማድረግ እውቀቱን ያካፍላል፣ይሰጣል ያስተምራል። ምን መናገር፣ስለምን ምን ማቅረብና ማተት እንዳለበት ቀድሞ ማወቅና መረዳት፣ ጥናት ማድረግና የተጠኑ ጉዳዮችን በመረጃ ማቅረብ ከአስፈላጊነቱም በላይ ብልጠትና ጥበብ ነው ።

አንድ ኢትዮጵያዊ ማንነቱን እንደ ኢትዮጵዊ ኅብረተሰብ ማንነት ጠንቅቆ በመረዳትና በማወቅ ሊናገር፣ ሊያስረዳና ሊያሳስብ ይችላል።ኢትዮጵያ እጅግ ታላቅ፣ ጥንታዊ፣ሰፊና ውስብስብ ጥልቅ ታሪክ፣ በባህልና ልዩ ኅብረተሰባዊ አንክሮ አመለካትና አሰተዋይነት ያለው ሕዝብን የያዘች አገር ናት። ኢትዮጵያ አሀዳዊ አገር፣ አንድ ብሔራዊ ኅብረተሰብ፣ የግዛት አንድነት ዳር ድንበር ያላት፣ልዩ መታወቂያዋ አረንጓዴ _ቢጫ _ቀይ ሰንደቅ ዓላማ፣በማንነት ልዩ ፀባይ በኢትዮጵያዊነት የምትገለጽና ለዓለም በነፃነት ትግሏ አርአያነት ኢትዮጵያኒዝምን ያተረፈች ክቡርና ውድ አገር ነች።

አንተ ፕ/ር አል ገ/ማሪያም አውቀህም ሆነ ሳታውቅ አጻጻፍ፣አነጋገርህና አካሄድ ሁሉ ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያዊነት የሚበጅ ነገር ይዘህ አይደለም። አንደኛ ብሔራዊ (ኔሽን) እና ኮሚኒቲን ወይም ማህበረሰብን እንዴት መጠቀምና መግለጽ እንዳለብህ አልተረዳህም። ኢትዮጵያ አገር ፣ሕዝቧም ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማ ያለው ትልቅ እንጂ በትንሽ ኮሚኒቲ ነጠላ አጠራር አትሰየምም።ይህ ትልቅ ስህተት ነው እኔን ብቻ ሳይሆን ብዙ ሰዎችን እንዳስቆጣ ተረዳው።እንዴት ብትደፍር በእደዚህ ሁኔታ ለመግለጽ እንደፈለግህ አልገባኝም? ተልዕኮው ከምን የተነሳና ምን ፍሊጋ ነው?

ሁለተኛውና ዋናው ለዚህ ጹሁፍ መነሻዬ የሆነው የሕዝብን የአገር ባለቤትነት በቁጥር ብዛት፣በእድሜና በጾታ እያልህ የምትከፋፍለው የፖለቲካ ወልጋዳነትና ፀረ_ ኢትዮጵያዊነት አካሄድ ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ በአንድነቱ፣በኅብረት ለአህዳዊ ኢትዮጵያ፣ ለነፃነቱ፣ ለትክክል እኩል መብቱ ትናንትም _ዛሬም በአንድነት የቆመና የታገለ ፣ ዛሬም_ ነገም የሚያደርገውና የሚፈጽመው ታሪካዊ ግዳጁና ኃላፊነቱ ነው። ይህን ታሪክ ወንድሜ ብታውቅ መልካም ነው ።ከአገኘህው ጋር አትሰለፍ፣ ቀድመህም አትሂድ።

የአሜሪካንን ታሪክ፣የመንግሥት ሥርዓትና ሕገ_ መንግሥትን ሙያህ በማድረግ እያስተማርክ ያለህ መምህር ነህ።የአሜርካን አገራዊነት ወይንም መንግሥትነት የተገኘው በወጣት፣ አዛውት በጾታ ተከፋፍለው አይደለም። የአሜሪካ መስራች አባቶች ወጣቶች የአንድ እድሜ ክልል ትውልድ ሆነው አይደለም።በእድሜ ክልል ልዩነት ፈጥረው ሳይሆን ሁሉም በአንድነት በአገር መርሆ መሰረት ላይ መክረውና አስበው የሚበጀውን በተገባር በመፈጸም ነው አገራቸውን ዛሬ ለአለችበት ምሳሌነት ያበቁት። የአሜሪካ መስራች አባቶች ቤንጃሚን ፍራንክልን ከነ ጆን አዳምና ቶማስ ጃፈርሰን በትንሹ የ40 ዓመት የአባትና ልጅ ልዩነት ነበራቸው።ሌሎችም እንደዚሁ የዕድሜ ልዩነት ቢኖርም በአገር ጉዳይ በጋራ ተከባብረው አሳብ ተለዋውጠው ሁሉም የችሎታውን በማበርከት ተግባራዊ በማድረግ እንጂ አንተ እንደምትመድበው ዓይነት በእንሰሳ አልተጠራሩም። ቺታ ና ሂፖ አላሉም ወይንም ዝሆንና አህያ ሆነው አይምሰልህ ። ሽማግሌ ወጣት፣አዝጋሚ ፈጣን ፣ወንድ ሴት፣የሚባል ልዩነት በዜጐች መሀል፣ በአገር ጉዳይ ውስጥ የለም።ይህን ማስብና ለሕዝብ ማቅረብ እጅግ ግብዝነት ከመሆኑ ጋር ለወያኔ የከፋፋይ ሥርዓት የሚጠቅም አካሄድ ነው። ለአንተም ለሰማያዊ ፓርቲም አይጠቅምም።በዚህ ልታፍርና ልትጸጸት ይገባሃል።

ወጣቱ ለአገሩ፣ ለነፃነቱ፣ለዜግነቱና ለመኖሩ ዋስትናው ሳያሰልስ መታገል የሚኖርበት ሃቅ ነው።ይህ እንዲሆን ምንጊዜም የሚሰጥና የሚበረታታ አሳብና በየትውልዱም የሚጠበቅ ተግባር ነው። ሰማያዊ ፓርቲ ጠንክሮና በርትቶ ወያኔን ማሶገድ የሚችልበት ጉልበትና አቅም ከአገኘ እሰየሁ ነው። ነገር ግን ሰማያዊ ፓርቲ የተቋቋመው የወያኔን ሕገ_ ወጥ ሕገ_ መንግሥት ተቀብሎ፣ ሕግ_ መንግሥቱም ይከበር እያለ ወያኔ የሚለውን ሁሉ ተቀብሎ  እንደ ዴሞክራሲም ስርዓት በምርጫ ለመወዳዳር ነው።

የወያኔንና ሻቢያን ዘረኛ ከፋፋይ አቋሙንና የአጋሚዶ የኃይል ባህሪን ገና ከጅምሩ አምርረውና አክርረው የተቃወሙና ያወገዙ እውነተኛ የሃቅ የኢትዮጵያ ልጆች በግንባር ቀደምትነት ታግለዋል።ከነዚህም ውስጥ ወያኔ ያለማቋረጥ ያንገላታቸው፣ ደጋግሞም በእስርና በፍርድ ቤት ያመላለሳቸ፣ያሰቃያቸው ለኢትዮጵያ አህዳዊ፣ ለሕዝቧ ኅብረተሰባዊ ትስስርና አንድነት ፣ለታሪካ መልካምና ክብርነት፣ ከዚህም የተነሳ የሕዝብን ተቀባይነት አግኝቶ አገርን መረጋጋት ተሰፋ የሰጠ አርቆ አሳቢና ጥበበኛ ቆራጥና ፅናት ያለው አንጋፋው ፕሮፌሰር አስራት ወ/የስ ሕይወትን በትግል አሳልፈዋል።ሌሎችም እስከ አሁን ለአገር አንድነት፣ ለሕዝብ ደህንነት ከወያኔ ጋር እየተፋለሙ ያሉ እነ ኢንጅነር ኃይሉ ሻውል፣ ሻለቃ ጌታቸው መንግስቴ፣ በእሰር ቤት የሚሰቃዮ አቶ ስለሽ ሙላቱና እጅግ ብዙ በቀዳሚነት ተነሳስተው አመመን ደከመን፣ ሸመገልን ሳይሉ በፅናት በመቆም ለአገር ተረካቢው ወጣት አርአያ ለመሆንና ኃላፊነትን ለመወጣት ነው።ኢሕአፓ ወንድ ሴት፣ወጣት ሽማግሌ ሳይል ሁሉን ለአገሩ አንድነት ድርሻውን እንድወጣ ትናንት _ ዛሬ_ ወደፊትም የሚታገሉ የቆሰሉ ፣የደሙ አንጋፋዎችን ያካተተ ድርጅት ነው። አንድ ድርጅት የሚለካው የሚጠበቀውን ውጤት ማግኘቱ ብቻ ሳይሆን በቆራጥነትና በፅናት ቆሞ መታገሉና ትውልዱን ማሳየቱና ማስተማሩ ነው። እነዚህን መሰል ግለሰቦችና ድር ጅቶች መልካም ምሳሌነት በሌላቸውና በተለያዮ እንሰሶች በቺታና ሂፖ መግለጽህና ማስመሰል  አግባብነት የሌለው ከመሆኑ ጋር የወያኔ ባህሪና ጠቀሜታውም ለወያኔ ነው።

የኢዮጵያ ሕዝብ ልዩነት ሳይፈጥር እከሌ ከእከሌ ሳይባባል በአቅሙና በችሎታው ወንድ ሴት፣ ልጅ አዋቂ (ሽማግሌ_ አሮጊት) ሳይባባል በኅብረት በቆራጥነት ሁሉም ለአገሩ በክተት አንድነት ኃይል ተሳስሮ በመቆምና ተግቶ በመስራቱ ኢትዮጵያን በነፃነት በመጠብቅ ደህንነቱን አስከብሮና ታፍሮ የኖረ ለዚህም መገለጫ ኢትዮጵያዊነት ያተረፈ ሕዝብ ከመሆን ጋር ለዓለም ኅብረተስብም ኢትዮጵያ ያበረከተችው በአካል መገኘት፣መልካም ሰብዓዊነት፣ ለነፃነት አጋርነት ኢትዮጵያንዝምን ምሳሌነት አገኝታለች።

ስለዚህ የኢትዮጵያ ታላቅነት በኅብረትና በጋራ መቆም ኃይላችንና ድላችን ስለሆነ በአንድነት ሁላችንም ዛሬም_ ወደፊትም እንደ ትናንቱ ቀደምት ትውልዳችን እንቆማለን። በቺታና ሂፖ አትስይመን። አንተም ኢትዮጵያና ሕዝቧን እወቅ ተረዳ። ለኢትዮጵያ ቅን አመለካከት ካለህና መልካም ማድረግ ከፈለክ፣ አንተ የኢትዮሜድያ ደህረ ገጽ ኤድተርነህ ለምን ነው ወያኔን የሚቃወሙና የሚነቅፉ ጹሁፎች በዚህ ደህረ ገጽ የማይወጡት? እስቲ ይህ አንተን ጭምር የሚቃውመውን ቅንነትና ድፍረቱ ካለህ ይለጠፍ እንይ።

በጨረሻም የማሳስብህ ኢትዮጵያዊነት ከማንም ከምንም በላይ በአንድነት የነፃነት፣ የዜግነት መብት ክብርና ኩራት ትልቅነትና መታፈሪያም ነው። ይህን ክቡር ጸጋ ለመከፋፈል ባትዳፈረው ጥሩ ነው። የፈለግከውን ድርጅት መደገፍ መብትህ የተጠበቀ ነው።ነገር ግን የኢትዮጵያን የፖለቲካ ሁኔታ ማዛባትና ማጣመም ወይንም ለማበላሸት መሞከር ጥፋት ሰለሆነ በሕግ የሚያሰጠይቅ ይሆናል፣ ለኢትዮጵያ ጉዳይ ተቆርቋሪዎች አሉ። አሰብበት እያልኩ አሳቤን አካፍላለሁ።

## ምንጊዜም ኢትዮጵያ ! !!